# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 196 የካቲት 8 2004 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**በግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት መለስ ከሥልጣኑ እስካልተባረረ ድረስ በፋሽስታዊ አገዛዙ መበደላችን ብቻ ሳይሆን ባልተገሩ ንግግሮቹ ማፈራችንም ይቀጥላል። የመለስ ውሸቶች፤ የትዕቢትና የብልግና ንግግሮች የሚቆሙት የመለስ ዜናዊ ሥልጣን ሲያበቃ ብቻ ነው። ይህንን ማድረግ ደግሞ የሁላችንም ኃላፊነት ነው።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የመለስ ዜናዊ የሳተላይ አፈና አረብ ሳትን አሳስቧል፤ ለሊባኖስ አዲስ ገበያ ፈጥሯል

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የአረብሳትን የሳተላይት ቴሌቪዥን ስርጭቶችን እያወከ መሆኑን የሊባኖስ የቴሌኮሚኒኬሽን ሚኒስትር ኒኮላስ ሲህናው ደይሊ ስታር ለተባለው ጋዜጣ ገለጹ።

ሚንስቴሩ የአረብሳት ባለስልጣናት የኢትዮጵያ መንግስት ስርጭቶቹን ከመጥለፍ ተግባሩ እንዲገታ የጠየቁበትን ደብዳቤ ማግኘታቸውን ገልጸው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ አገዛዙ እያካሄደ ላለው የሞገድ ጠለፋ ምክንያት መሆኑን አስምረውበታል።

የሊቢያ እና የግብጽ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአረብ ሳትና በናይል ሳት የሚተላለፉ አልጀዚራን ጨምሮ በርካታ ስርጭቶች እየታፈኑ መሆኑን የጠቀሱት ሚንስቴር ኒኮላስ አረብሳት የገጠመውን ችግር ለዘለቄታው እንዲወጣ ሊባኖስ አዳዲስ ፍሪኬንሲዎችን ትሰጣለች ብለዋል።

በአረብ አገሮች በተፈጠረው የለውጥ ንቅናቄ የተደናገጡ አገዛዞች በሳታላይት ስርጭት ሞገዶች ላይ የሚፈጽሙትን ጠለፋ መቋቋም የሚችል አቅም እንደሚፈጥሩ የተናገሩት ሚንስቴር ኒኮላስ፤ ሊባኖስ የመለስ ዜናዊ የሞገድ አፈና የፈጠራለትን ገበያ ለመጠቀም “ለአረብ ሳት ጥቃት የሌለበት ገነት እንፈጥራለን” ሲሉ ዝተዋል።

ከዚህ በፊት ኢሳት በሚል ምህፃረ ቃል የሚታወቀውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንን ለማፈን ሲል የመለስ አገዛዝ የራሱን ኢቲቪ በማፈኑ ኢቲቪ “አጥፍቶ ጠፊ” የሚል ስያሜ አግኝቶ እንደነበረ ይታወሳል። በቅርቡ ደግሞ በተመሳሳይ መንገድ የኤርትራ ቴሌቪዥንን ለማጥፋት ሲማስን ራሱን አጥፍቷል።

በዚህ ህገወጥ ድርጊት የተበሳጨው አረብ ሳት ቅሬታውን ለመለስ ዜናዊ መንግሥት ቢጽፍም አጥጋቢ ምላሽ ባለማግኘቱ ጉዳዩን ወደ ዓለም ዓቀፍ ዳኝነት ሊመራው እንደሆነ ገልጿል።

የመለስ ዜናዊ አፈና ከኢትዮጵያዊያን አልፎ ሌሎች አገሮችንና ኩባንያዎችን እያሳሰበ መሆኑ ይህ አንዱ ተጨባጭ ማስረጃ ነው ይላሉ ታዛቢዎች።

## በአማራ ክልል የሚገኙ መምህራን በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ መግለጽ መጀመራቸው ተዘገበ። የክልሉ መምህራን ማህበር ሊቀመንበር በወያኔ ታግተዋል

በየጊዜው እየናረ በሄደው የኑሮ ውድነት ምክንያት የደመውዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸው በአግባቡ ሲጠይቁ የቆዩ የአማራ ክልል መምህራን ከአገዛዙ ምንም መልስ ሊያገኙ ባለመቻላቸው ተቃውሞአቸውን በተለያየ መንገድ እየገለጹ መሆኑን ከስፍራው የሚደርሱን ዘገባዎች አረጋገጡ።

በክልሉ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ካለፈው የትምህርተ አመት ጀምሮ ጥያቄያቸውን በተዋረድ ለክልሉ ከዚያም አልፈው ለፌደራሉ ትምህርት ቢሮ ያቀረቡ ቢሆንም ሁሉንም በሃይል ጸጥ አድርጎ በመግዛት ጡንቻው የሚተማመነው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ ቡድን ለመምህራኑ ጥያቄ ጆሮ ዳባ ከማለቱም በላይ ጥያቄውን የሚያስነሱ የሽብርተኛ ድርጅቶች ተላላኪዎች ናቸው በማለት ሲያስፈራፈራራ መቆየቱ መዘገቡ ይታወሳል።

ከወያኔ የክልል ቢሮ ሃላፊዎች የሚሰጣቸውን ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ ወደጎን በመተው ባለፈው ማክሰኞ በሰሜን ጎንደር የደባርቅ መምህራን ለአንድ ቀን ትምህርት ማቆማቸው ሲታወቅ በአካባቢው የተለያዩ ወረዳዎች የሚገኙ ሌልች ትምህርት ቤቶችም ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ እየዛቱ እንደሆነ ታውቆአል።

የአማራ ክልል መምህራን ከደመውዝ ጭማሪዉ በተጨማሪ የወያኔ አባል ባልሆኑ መምህራን ላይ በደረጃ እድገትና በሙያ ሥልጠና ዘርፍ የሚደርሰው አድልዎና ጭቆና እንዲቆም ይጠይቃሉ። በመምህራኑ ጥያቄ ደስተኛ ያልሆነው የወያኔ አገዛዝ የክልሉን መምህራን ማህበር ሊቀመንበር የሆኑትን መምህር መንግሥቱ አህመዴን ለረጅም ጊዜ ሲያስፈራራ ከቆየ ቦኋላ ሰሞኑን አንዳገታቸው ለማወቅ ተችሎአል።

መምህር መንግሥቱ አህመዴ በሆዳቸው ጥቅም ተገዝተው ከወያኔ ጋር አገር አያፈረሱ ያሉትን ባለሥልጣናት ባለመቀላቀል ለመምህሩ መብትና ጥቅም የሚሟገቱ በዚህም ስራቸው በመላው የክልሉ መምህራን ዘንድ ፍቅርና አድናቆት የተቸሩ የሙያ ሰው እንደሆኑ የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በባርነት ወደ ሳውዲያረቢያ ለሚልካቸው ዜጎች በየቀኑ እስከ 1500 ቪዛ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን የሳውዲ ኤምባሲ አስታወቀ

አዲስ አበባ የሚገኘው የሳዊዲ አረቢያ ኤምባሲ የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ማግስት ጀምሮ ወጣት ሴቶችን በተጭበረበረና ከእውነት በራቀ ተስፋ ከቤት እያስኮበለሉ ወደ አረብ አገሮች በመላክ ከፍተኛ ትርፍ ሲያግበሰብሱ የኖሩና ቁጥራቸው ከ150 በላይ የሆኑ የወያኔ የድለላ ኤጀንሲዎችን በኤምባሲው የስብሰባ አዳራሽ ስብስቦ ይፋ እንዳደረገው በየቀኑ ቁጥራቸው እስከ 1500 ለሚሆኑ በባርነት ወደ አገሩ ለሚላኩ ሰዎች ቪዛ ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅት ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ተጀምሮአል።

ሪፖርተር የተባለው አፍቃሪ ወያኔ ጋዜጣ ዜናውን እንደዘገበው ፤ ካለፈው ሰኞ ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆነው አዲሱ መመርያ፣ አገር ውስጥ ሆነው ዜጎችን ለግርድና ወደ ሳውዲ የሚሊኩትና እዚያው ሳውዲ ሆነው የተላኩትን በየባሪያ አሳዳሪዎች ቤት የሚያከፋፍሉ ኤጀንሲዎች የተቀናጀ ሥራ መሥራት የሚጠበቅባቸው ሲሆን በኢትዮጵያ ያለው ኤጀንሲ አንዲት ሠራተኛ ለመላክ ከተላኪዋ ጋር ከተስማሙና ለኤምባሲው ካሳወቁ በኋላ ልጅቱ አልሄድም ብትል ወይም ሳዑዲ ከሄደች በኋላ ብትጠፉ ተጠያቂው ኤጀንሲው እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡

ወያኔ በፈጠረው የኢኮኖሚ ችግር በአገራቸው ተስፋ ቆርጠው ለግርድና ሥራ ወደ አረብ አገር ለመሄድ አንዴ ከተስማሙ ቦኋላ በሌሎች እህቶቻቸው ላይ የደረሰውን ችግር ሰምተው ሃሳባቸውን ቢቀይሩ እንኳ አፍንጫቸውን ተይዘው ሊሰጡ እንደሚገባ የሚደነግገው ይህ የሳውዲ ኤምባሲ መመሪያ ሰለባዎቹ እዚያ ከደረሱ ቦኋላም ቢሆን የተሻለ አማራጭ ፍለጋ ከኤጀንሲዎቹ ውጪ ዕድላቸውን እንዳይሞክሩ አጥብቆ ይከለክላል።

ወያኔ 17 አመት ባደረገው የበረሃ ውጊያ በለስ ቀንቶት ሥልጣን እስከተቆጣጠረበት 1983 ዓ/ም ድረስ ወደ አረብ አገር ለግርድና ሥራ የሚላክ አንድም ኢትዮጵያዊ እንዳልነበረ የሚያስታውሱ ሃይሎች፤ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ስልጣን ተቆጣጥርኩ እያለ የሚደሰኩረው የትግራይ ገዢ ጉጂሌ ወጣት እህቶቻችንን ከድህነት ለከፋ ባርነት አሳልፎ በመስጠት የአገርና የህዝብ ጠላትነቱን አረጋግጦአል ይላሉ።

ላለፉት በርካታ አመታት ወያኔ ወደ አረብ አገር በግርድና እየላካቸው ያሉት ሙሉ በሙሉ በለጋ የወጣትንነት ዕድሜ ክልል የሚገኙ የሚንከባከቧቸውና ኮትኩቶ የሚያሳድጋቸው አገርና መንግሥት ቢያገኙ የነገው የአገሪቱ ተረካቢ ሊሆኑ የሚችሉ ብሩህ አእምሮና ጉልበት ያላቸው ናቸው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ የቀድሞ ሰራዊት አባላትን እና በጡረታ የተገለሉ ተቀናሽ ሰራዊት አባላትን ወደ መከላከያ ለመመለስ እየዳከረ መሆኑ ተዘገበ

የአገዛዝ ዘመናቸውን ዕድሜ ለማራዘም ባላቸው ጭንቀት የተረጋጉ ሲመስላቸው ወታደር በመቀነስ በአገሪቱ ስለሰፈነው ሰላምና መረጋጋት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የሚያስጮሁ፤ ህዝባዊ ተቃውሞ ሲያይልባቸው ደግሞ ከፍርሃት በመነጨ ውሳኔ የበተኑትን ወታደር መልሶ ለመስብሰባ መራወጥን እንደሙያዊ ተግባር የሚቆጥሩት የወያኔ ቁንጮዎች፤ ቀደም ሲል ከአገሪቱ መከላኪያ የተባረሩትን የጦር አባላት እንዲሰባሰቡ ሰሞኑን ጥረት በማድረግ ላይ እንዳሉ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ዜና ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን መረጃ ሰሞኑን በሰሜን ሸዋ ዞን 167 ተቀናሽ የሰራዊት አባላት በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ተስብስበው እንደነበርና የተቀናሽ ሰራዊት አባላት ወደ መከላከያ እንዲመለሱ ከደብረ ዘይት አየር ሀይል አባላት የተውጣጡ መኮንኖች ለማሳመን ጥረት ቢያደርጉም፣ ሁሉም አባላቱ በአንድነት ጦርነት ሲኖር ወይም ዝግጅት ስትፈልጉ ብቻ ነው ወይ የምትፈልጉን በማለት የቀረበላቸውን ጥሪ ለመቀበል ፍቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጸዋል።

በአገዛዙ የጅል አይሉት የአዋቂ ብልጣ ብልጥነት የተናደዱት ወታደሮች ለሰበሰቡዋቸው የወያኔ ተላላኪዎች በርካታ ችግሮችን ፊት ለፊት ያለምንም ፍርሃትና ጭንቀት መናገራቸውን የዘገበው ዘጋቢያችን "አንድ ጊዜ በባድሜ ትምህርት አግኝተናል፣ ለሁለተኛ ጊዜ ግን አንሞኝም፣ እኛ እንደዜጋ እየታየን አይደለም፣ ጡረታችንን ከፈለጋችሁ መውሰድ ትችላላችሁ" እስከማለት እንደደረሱና ሁሉም እልህና ቁጭት ፊታቸው ላይ ይታይ እንደነበር መረዳቱን ገልጾአል።

ወያኔ ተቀናሽ የቀድሞ ሰራዊት አባላቱን በአገር ፍቅር ሰሜት ለመማረክ "ኤርትራ በአገራችን ላይ ለመዝመት አቅዳለችና አገራችሁን የመከላከል ታሪካዊና የዜግነት ሃላፊነት አለባችሁ “የተባሉ ቢሆንም በአገር ጉዳይ ወያኔ የሚያደርገው የአዞ እንባ የማንንም ልብ ሊያማልል እንዳልቻለ ታውቆአል። በቀድሞ ሰራዊቱ ምላሽ የተደናገጡት ከአገዛዙ ፌደራል ተብዬ መሥሪያቤት ተወክለው (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ፍየል ወዲህ፤ ቅዝምዝም ወዲያ

ሰሞኑን መለስ ዜናዊ እንደተለመደው አራምባና ቆቦ የረገጡ ነገሮችን በአሻንጉሊት ፓርላማ በኩል ለሚጠላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተላልፏል። መለስ የሚናገራቸው ነገሮች በሙሉ በውሸትና በትዕቢት የተሞሉ መሆናቸው የተለመደ ነው። አሁን ግን ከዚያም ብሶ እንደ አዕምሮ ህመምተኛ የማይገናኙ ነገሮችን ሲያገናኝ ተስተውሏል። በዚህም ምክንያት ንግግሩ ሁሉ “ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ” የሚሉት ዓይነት ሆኗል። በዚህ ግራ የተጋባ ንግግሩ ውስጥ በተለይ ስለ ጋዜጠኞች አያያዝ ኢትዮጵያንና እንግሊዝን ወደ አወዳደረበት ዓረፍተ ነገር እናመራለን።

መለስ “የፀረ-ሽብር” ህጉ በዓለም ላይ ከሚገኙ ምርጥ ህጎች ውስጥ ምርጥ ምርጥ አንቀጾች ብቻ እየተለቀሙ የሰፈሩበት መሆኑን ገለፀ። እንዲያውም ምርጦቹ ዓረፍተ ነገሮቹ አንዳችም ለውጥ ሳይደረግባቸው መገልበጣቸው በኩራት ተናገረ። በዚህ ህግ መዳኘት መታደል የሆነ ያህል ስለህጉ “ምርጥነት” ብዙ አስገራሚ ነገሮችን ተናገረ። ቀጥሎም እንዲህ ዓይነቱን ህግ ለማግኘት ባልታደለችው እንግሊዝ አገር ውስጥ የሚገኙ ጋዜጠኞች የታዋቂ ግለሰቦችን ስልኮች በመጥለፋቸው ለእስር መዳረጋቸውን ገለጸ። “እኛ ዘንድ ግን ጋዜጠኞችን ያሰርነው ከሽብርተኞች ጋር ሲተባበሩ እጅ ከፍንጅ ስንይዛቸው ነው” ሲልም ተናገረ። ይህን ነው ፍየል ወዲህ፤ ቅዝምዝም ወዲያ የሚባለው።

ለመሆኑ መኮረጅ የሚያኮራ ነገር ነው? ደግሞስ፣ ሥራ ላይ የማይውል ከሆነ ምርጥ ህግ ኖረ አልኖረ ምን ፋይዳ አለው? በህገ መንግሥቱ የተፃፉት መብቶች አንዳቸውም በሥራ ላይ የማይውሉ በመሆኑ አይደለም እንዴ “ምናለ ወረቀት ባትጨርሱ” እየተባለ ያለው?

እውነታው የመለስ ዜናዊ “የፀረ - ሽብር” ህግ ህገ አራዊትነትን ህጋዊ የሚያደርግ መሆኑ ነው። ለዚህም ነው በአገር ውስጥም በውጭ አገርም ተቃውሞ የበዛበት።

ለመሆኑ እንግሊዝ አገር የግለሰቦችን ስልክ በመጥለፋቸው ጋዜጠኞች የተጠየቁት፤ ጥቂቶችም የታሰሩት ለምንድነው? ምክንያቱ እንግሊዝ አገር የግለሰብ ምስጢር የተከበረ ስለሆነ ነው። ዜና ለማግኘት ሲባል የግለሰብን ምስጢር በህገወጥ መንገድ ማግኘት ወንጀል ነው። የእንግሊዝ መንግሥት የዜጎቹን መብት ለማስከበር ሲል ህገወጥ የምስጢር ዘረፋን መከላከሉ ተገቢ ነው።

### ኢትዮጵያ ውስጥስ?

መለስ በሚገዛት ኢትዮጵያ የግለሰቦች ምስጢር የሚደፈረው በጋዜጠኞች ሳይሆን በመለስ ዜናዊ ሰላዮችና ጆሮጠቢዎች ነው። የመለስ ዜናዊ ሰላዮች ጆሮዎቻቸውን በሰዎች ስልክና አንደበት ላይ እንደደቀኑ ውለው ያድራሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ እየሆነ ያለውና እንግሊዝ አገር የሆነው የሚያመሳስላቸው ነገር የለም።

ኢትዮጵያ ውስጥ ጋዜጠኞች የሚታሰሩት፣ የሚገረፉት፣ ለዓመታት እስር የሚዳረጉት እውነትን በመናገራቸው፤ አገራቸውን በመውደዳቸው እና መለስ ዜናዊን በመቃወማቸው ነው። ርዕዮት ዓለሙና እስክንድር ነጋ እንዲሁም በመለስ ዜናዊ እስር ቤት እየማቀቁ ካሉት ጋዜጠኞች አንዳቸውም የግለሰቦችን ምስጢር በህገወጥ መንገድ ለማግኘት አልጣሩም። እነሱ የፃፉት ስለፍትህ፣ ስለአንድነት፣ ስለ ነፃነት እና ስለዲሞክራሲ ነው። ይህ ሥራቸው ነው በመለስ ዜናዊ ፍርደ ገምድል ችሎት “ሽብርተኛ” ያስባላቸው። “አዛኝ ቅቤ አንጓች” እንዲሉ በዓለም በፀረ-ጋዜጠኝነቱ ግንባር ቀደም የሆነው መለስ ዜናዊ ለእንግሊዝ ጋዜጠኞች አዛኝ መስሎ መቅረቡ የሚገርም ነው።

መለስ ዜናዊ በጉልበት ከያዘው ስልጣን ካልተባበረ በስተቀር የማይመሳሰሉ ነገሮችን እያመሳሰለ የዋህ አድማጮችን ለማደናበር መሞከሩ የማይቀር ነው። ባልተገራ አንደበቱ ሕዝብን እየዘለፈ ራሱን የፍትህ፣ የዲሞክራሲ እና የልማት አባት አድርጎ ለመሾም የሚያደርገውን መወራጨት በአንክሮ መከታተልና ማጋለጥ ይገባል።

በግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት መለስ ከሥልጣኑ እስካልተባረረ ድረስ በፋሽስታዊ አገዛዙ መበደላችን ብቻ ሳይሆን ባልተገሩ ንግግሮቹ ማፈራችንም ይቀጥላል። የመለስ ውሸቶች፤ የትዕቢትና የብልግና ንግግሮች የሚቆሙት የመለስ ዜናዊ ሥልጣን ሲያበቃ ብቻ ነው። ይህንን ማድረግ ደግሞ የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ሶማሊያውያን ማህበር ወያኔ በኦጋዴን ህዝብ ላይ የሚፈጽመው ወንጀል እንዲጣራ ለደቡብ አፍሪካ ጠቅላይ አቃቢ ህግና ለአለማቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት አመለከተ

አልጀዚራ እንደዘገበው የደቡብ አፍሪካ የመገናኛ ኔት ወርክ የተባለ ተቋም የአለማቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት በኦጋዴን ህዝብ ላይ የሚፈጸመው ወነጀል እንዲጣራ ጠይቋል።

የመለስ ዜናዊ ወታደሮች ፈጽመዋል ከተባለው ወንጀሎች መካከል ያለ ፍርድ ቤት ሰዎችን መግደል፣ ማሰር፣ ማሰቃየት፣ የሰዎችን አድራሻ ማጥፋት፣ ሴቶችን መድፈር፣ ቤቶችን ማቃጠል፣ እንስሳትን ማጥፋት እና አካባቢን ማውደም የሚሉት ይገኙበታል።

ፋዴል ሙህመድ አብዱላሂ የተባለ የኦጋዴን ተወላጅ እንደተናገረው ደቡብ አፍሪካ ህግን እና ሰብአዊ መብቶችን በማክበር በኩል ምሳሌ ልትሆን የምትችል አገር በመሆኑዋ፣ እንዲህ አይነት አቤቱታ ለማቅረብ ተመራጭ አገር ናት።

700 ገጽ የሚሆኑ ማስረጃዎች ለጠቅላይ አቃቢ ህግ መሰጠቱ ታውቋል።

የመለስ ዜናዊ አፈቀላጤ የሆነው የበረከት ስምኦን መስሪያ ቤት እስካሁን ድረስ እንዲህ አይነት ክስ መቅረቡን እንደማያውቅ ተናግሯል። የኦጋዴን ተወላጆች ማህበር ባወጣው መግለጫ እንዳመለከተው በአሁኑ ሰዓት ከ20 ሺ በላይ የአካባቢው ተወላጆች በ200 እስር ቤቶች ውስጥ ቁም ስቅላቸውን እየተቀበሉ ናቸው።

አልጀዚራ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ወታደሮች በኦጋዴን ህዝብ ላይ የፈጸሙትን ወንጀል ሂውማን ራይትስን ጨምሮ በርካታ አለማቀፍ ድርጅቶች ማውገዛቸውን ጠቅሷል።

በጉዳዩ ላይ የአለማቀፉ ወንጀለኞች ፍርድ ቤት የሰጠው አስተያየት የለም፣ ይሁን እንጅ ፍርድ ቤቱ በመላው አለም በሺዎች የሚቆጠሩ አቤቱታዎች የሚቀርቡለት በመሆኑን፣ አቤቱታዎችን ሁሉ ለማየት ረጅም ጊዜ እንደሚወስድ ተመልክቷል።

## መድረክ የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ህዝባችንን ንብረት አልባ ለማድረግ ባወጣው አዲሱ የመሬት ሊዝ አዋጅ ላይ ከህዝብ ጋር መወያየቱ ተዘገበ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ህዝባችንን ንብረት አልባ ለማድረግ ባወጣው አዋጅ ላይ ከህዝብ ጋር ለመወይየት ላለፈው ዕሁድ የካቲት 4 2004 ዓ.ም ጠርቶት የነበረው ህዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ መካሄዱን ስብሰባውን የተሳተፈው ዘጋቢያችን ከስፍራው ባስተላለፈው ዜና ገለጸ።

መድረክ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ጽ/ ቤት አዳራሽ ባደረገው በዚህ ስብሰባ ቁጥራቸው ከ1000 በላይ የሆኑ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የተሳተፉ መሆኑን የገለጸው ዘጋቢያችን የመድረክ አመራር አባል የሆኑት አቶ ገብሩ አስራትና አቶ ግርማ ሰይፉ በጥናት ላይ የተመሰረተና ለውይይቱ መነሻ የሚሆን ጽሁፎችን አቅርበው እንደነበረ ዘግቦአል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ስብሰባው በተካሄደበት የወረዳ 5 ጽ|ቤት አካባቢ ስብሰባው ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ በርካታ የፌዴራል ፖልሶችና ስቪል የለበሱ የወያኔ የጸጥታ ሰራተኞች ተሰማርተው ነበር። በስፍራው ከተሰማሩት የፌዴራል ፖልሶች አንዱ ለዘጋቢያችን እንደገለጸው ህዝብ በአዳራሹ አካባቢ የሚተረማመሱትን የፖሊስና የጸጥታ ሠራተኞችን ሲያይ ፈርቶ ወደ አዳራሹ ከመግባት ይታቀባል በዚህም መድረክ ህዝባዊ ስብሰባውን የጠራበት አላማ በህብረተሰቡ ውስጥ ምንም አይነት የድጋፍ መሠረት እንደሌለው እንዲያውቅ ይደረጋል የሚል የተሳሳተ ስሌት በአገዛዙ ቁንጮዎች አካባቢ ነበረ ብሎአል።

እነዚሁ ሲቪል የለበሱ የጸጥታ ሠራተኞች ወደ ስብሰባው አዳራሹ የሚያመሩትን ሰዎች እያስቆሙ ከመጠየቅ አለፈው ዛቻና ማስፈራርያ ቃላቶችንም ይሰነዝሩ ነበር ያለው ዘጋቢያችን አንድ ተሳታፊ ወደ አዳራሹ ሲመጡ የኢህአዴግ ካድሬዎች የማሸማቀቅ፣ የማስፈራራትና የማሳቀቅ ትንኮሳ እንዳደረጉባቸው ገልጸው፣ "ኢህአዴግ የዓመታት ይዞታችንን፣ መሬታችንን ነጥቆ የእናንተ ንብረት ጣራና ግርግዳ ብቻ ነው አለን፣ ወደ ፊት ሚስቶቻችንንስ እንደማይነጥቀን ምን ማረጋገጫ አለን?" በማለት በስብሰባው ላይ መናገራቸውን ገልጾአል።

የቀድሞ የህወሃት አመራር አባልና ከአረና ትግራይ መስራቾች አንዱ የሆኑት አቶ ገብሩ አስራት ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ፤ "የከተማን ቦታ በሊዝ ለመያዝ የወጣው አዋጅ ህገ መንግስትን የጣሰና ዜጎችን ለመቆጣጠር ያለመ ነው፣ ኢህአዴግ በኢኮኖሚ ራሱን የቻለን ማህበረሰብ ይፈራል፣ ምክንያቱም ይህ የህብረተሰብ ክፍል ለእርሱ የምርጫ ካርድ እንደማይሆነውና አብዮታዊ ዴሞክራሲ አመለካከቱን እንደማይቀበለው ያውቃልና፣ በዚህም ምክንያት ዜጎችን እያደኸየ የመግዛት ስትራቴጂ ይዟል" ብለዋል፡፡

መለስ ዜናዊና አንዳንድ የህወሃት አመራር አባላት ድርጅታቸው ላለፈው 20 አመታት በአገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ውስጥ ድጋፍ ሊያገኝ ያልቻለው በየከተሞቹ የሰፈረው ህዝብ በአብዛኛው አማራ ና የቀድሞ ሥርዓት ርዝራዦች በመሆናቸው ነው የሚል የጸና አቋም አላቸው። አዲሱ የከተማ ሊዝ አዋጅ የቀድሞ ባለንብረቶችን አፈናቅሎ ወያኔ በፈጠራቸው አዳዲስ ባለሃብቶች የመተካት ስውር አላማ እንዳለው ተደጋግሞ መዘገቡ ይታወሳል።

## የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ ከሥልጣን ማባረር ሃገራችንን ከድንቁርና ነፃ የማውጣት ትግል አካል ነው!!!

የሰለጠነ የሰው ኃይል ለልማት ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቀዳሚው መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። የልማት ፍሬዓማነት መለኪያ ከሆኑ አመልካቾችም አንዱ የሰለጠነ የሰው ኃይል የመፍጠር አቅም መገንባቱ ነው።

ሃገር እንድትበለጽግ ከተመጽዋችነትና የበታችነት መንፈስ መላቀቅና በራስ የመተማመን ስሜት መገንባት ይገባል። በራስ የመተማመን ስሜት የሚገነባው ደግሞ የራስ የሆነን ነገር በማክበር እና የራስን አቅም በመገንባት ነው። ይህም ደግሞ  የሰለጠነ የሰው ኃይል መገንባትን፤ የተገነባውን መንከባከብን እና በአግባቡ መጠቀምን ይጠይቃል።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ እየሆነ ያለው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ኢትዮጵያዊውን ባለሙያ አያምንም። ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ወይም ምሁር በጉጅሌው ካድሬዎች የሚንጓጠጥ፣ የሚጉላላ፣ የሚሰደብና የሚረገጥ እንጂ በአገሩ ጉዳይ የሚናገር፤ ስለ አገሩ የሚቆረቆር መሆን አይችልም። ኢትዮጵያዊ ባለሙያና ምሁር የካድሬ መጫወቻ ነው። የትግራዩ ጉጅሌ በጉልበት ሥልጣን ከያዘበት እለት ጀምሮ በእውቀትና በአዋቂዎች ላይ ዘምቷል።

እውቀትንና አዋቂዎችን ከማጥፋት ጎን ለጎን ደግሞ  የራሱን ትንሽነት መደበቂያ መንገድ ፈጥሯል። “እኔም የተማርኩና የተመራመርኩ ነኝ” በማለት የዝቅተኝነት መንፈሱን ለማስታመም ጉጅሌው ራሱን በግዢ በተገኙ የትምህርት ማስረጃዎች አንበሻብሿል። የሃገሪቱ የትምህርት ሥርዓትም እሱ ራሱ የያዛቸውን ዓይነት ባዶ ወረቀቶችን ማደያ አድርጎታል። በዚህም ምክንያት አገራችን ውስጥ ሙያም ባለሙያም ተዋርዷል። በዘመነ ወያኔ “የተማረ ነው” መባል የስድብ ያህል አሳፋሪ ሆኗል።

በእውቀትና በአዋቂዎች ላይ የተደረገው ዘመቻ ውጤት በየእለቱ እያየነው ነው:-

- ፍርድ ቤት ስንሄድ በስልክ እየተነገረው የሚፈርድ ዳኛ ችሎት ላይ ተኮፍሶ እናገኛለን፤
- የፍሳሽ ማውረጃ የሌላቸው ፎቆችን እየገነባ ያለ መሃንዲስ በጥበቡ ብዛት ይራቀቅብናል፤
- መርፌ በወጉ የማይወጉ ሃኪሞች በበሽተኞች ላይ ይዘባበናሉ፤
- ለተማሪዎቻቸው የሰጡትን ፈተና እራሳቸው ቢፈተኑ የማያልፉ መምህራን “ከኔ ባላይ ላሳር” ሲሉ ይገኛሉ።

በእንዲህ ዓይነት “የተማረ” ሰው ኃይል እድገት ሊመጣ ቀርቶ አሉበት መቆየትም አዳጋች ነገር ነው።

በአንፃሩ ቀድሞ የነበረው የትምህርት ሥርዓት በርካታ ድክመቶች የነበሩበት ቢሆንም በሙያቸው የተከበሩ ጥቂት ምሁራንን አፍርቷል። የመጀመሪያው አፍሪቃዊ አይሮፕላን አብራሪ፣ የመጀመሪያው አፍሪቃዊ የስልክ ቴክኖሎጂ ባለሙያ፣ የመጀመሪያዎቹ አፍሪካዊያን የስነ-መንግሥት ምሁራን ኢትዮጵያዊያን ነበሩ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብቻ ሳይሆን በቴክኒክ ኮሌጅ የሚሰጡ ትምህርቶች በሰለጠኑ አገሮች ከሚገኙ ተቋማት ጋር መሳ ለመሳ የሆነ ተቀባይነት ነበራቸው። ምሩቃኑም ሙያ ብቻ ሳይሆን የአገር ፍቅር ስሜት የተላበሱ ነበሩ። እነማንዴላን ጨምሮ  ኢትዮጵያ ለብዙ አፍሪካዊያን አርዓያ ነበረች። አሁንም ቢሆን የዚያ ወቅት አሻራ ያረፈባቸው ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች አሉ። እነዚህ ባለሙያዎች የሚገኙት ግን አሜሪካና አውሮፓ እና ሌሎች አገሮች ውስጥ እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም። ሙያቸውን ጠንቅቀው ያወቁ፤ በራሳቸው የሚተማመኑ ባለሙያዎች ሁሉ ተገፍተው አገር ለቀው እንዲሰደዱ በመደረጋቸው ኢትዮጵያ ልትመካባቸው የሚገቡ ባለሙያዎች የሚገኙት በውጭ አገራት ውስጥ ነው።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በየክልሉ ለህንፃዎች የዩኒቨርስቲነት ስያሜ መስጠቱን እናውቃለን። ወደ እነዚህ ህንፃዎች የሚመላለሰውም ወጣት ቁጥር በብዙ መጨመሩ እውነት ነው። ሆኖም ባለሙያ ሲያፈሩ ግን አልታዩም፤ ለዚህ ተግባር የተፈጠሩም አይደሉም።

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ያለበትን የእውቀት ማነስ የህዝብ ንብረት ለመሸጥ በምክንያትነት ሲያቀርብ መስማት ደግሞ ሌላው አስገራሚ ነገር ነው።

ለምሳሌ:-

- መሬትን በገፍ ለመሸጥ የሚያቀርበው ምክያት “ግብርናውን የማዘመን አቅምም ችሎታም የለንም” የሚለው እንደሆነ ልብ ይሏል። “ኢትዮጵያዊያን የግብርና ባለሙያዎች የት ገቡ?” ብሎ መጠየቅ አይቻልም። እንዲያም ሆኖ ግን “የግብርና ባለሙያዎችን በገፍ እያሰለጠንኩ ነው” እያለ ይቦተልካል።
- “የማዕድን ሃብታችን ለማልማት የሚጠይቀው እውቀትና አቅም የለንም” የሚለው ሰበብም ቱጃሩን እየጠቀመ እንደሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ዛሬ የአገራችን የወርቅ ማዕድን በቱጃሩ ግለሰብ እጅ ውስጥ ገብቷል።
- አሁን ደግሞ “የማኔጅመንት ባለሙያ የለንም” በሚል ሰበብ ኮርፓሬሽኖችን መሸጥ ተጀምሯል። የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ማኔጅመንት ለፈረንሳይ ኩባንያ መሰጠቱ በመሬት የተጀመረው ሽያጭ ወደ ኩባንያዎች የመምጣቱ መርዶ ነጋሪ ነው። የሚቀጥሉት ተረኞች የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እና የኤለክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን  እንደሚሆኑ መጠበቅ ይቻላል።

ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህ በድንቁርናው በመኮፈስ ላይ ያለው፤ ፀረ-እውቀት እና ፀረ-አዋቂ የሆነው የትግራዩን አምባገነን ገዢ ካስፈነብን የአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ነፃ እስካልወጣን ድረስ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ሊኖር ይችላል ብሎ አያምንም። ስለሆነም የትግራዩን አምባገነን ገዢ ጉጅሌ በጋራ አስወግደን ሃገራችን ከገባችበት የድንቁርና አዘቅት እናውጣ እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## በወያኔ የተሳሳተ ፖሊሲ ለሥራ አጥነት የተዳረጉ የአዲስ አበባ ወጣቶች የሚያዘወትሩባቸው ኳስና ፊልም ማሳያ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ወንጀሎች መበራከታቸውን የአገዛዙ ሹሞች ገለጹ

የገዢው ፓርቲ ልሳን የሆነው ሬዲዮ ፋና እንደገለጠው በ 4 ኪሎ፤ 22 ማዞሪያ ፤ ካሳንቺስ፤ 6 ኪሎና አውቶቡስ ተራ እንዲሁም ሳሪስ አካባቢዎች የሚገኙ የተለያዩ የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ጨዋታዎችንና ፊልሞችን እንደሚያሳዩ በየግድግዳዎቻቸው ላይ በግልፅ ማሳታወቂያ ለጥፈው በርካታ ወጣቶችን የሚያስተናግዱ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ወንጀሎች  ከጊዜ ወደጊዜ እየተበራከቱ መጥተዋል።

ከነዚህ የኳስ ማሳያ ቤቶች አንዳንዶቹ ከበስተጀርባቸው የጫት መቃሚያና የሺሻ ማጨሻ ሆነዋል የሚለው  የአዲስ አበባ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ምክትል ሀላፊ ታየ ጫላ ለፓርቲው ልሳን እንደተናገረው፣ በመርካቶ 7ኛ አካባቢ ባሉት ቪዲዮ ቤቶች ደግሞ ከባህል ውጭ የሆኑ የወሲብ ፊልሞች በግልጽ እንደሚታይባቸው አልሸሸገም።

የመንግሥት መናህሪያ በሆነቺው የአዲስ አበባ ከተማ ውስት በሚያስደንቅ ሁኔታ እየተበራከቱ የመጡ የቪዲዮ ማሳያ ቤቶች ውስጥ የሚታዩ ፊልሞች እስፔሻልና ኖርማል ተብለው በሁለት የተከፈሉ ሲሆን እስፔሻል የተባሉት ፊልሞች ወጣቱን የማደንዘዝ ሃይል ያላቸው የወሲብ ፊልሞች ናቸው። ከወሲብ ፊልሞች ውጪ ያሉት ኖርማል ተብለው እንደተለዩና ለመመልከት በፊልም አንድ ብር እንደሚከፈልባቸው እስፔሻል የተባሉት የወሲብ ፊልሞች ደግሞ ሁለት ብር እንደሚከፈልባቸው ተገልጾአል።

በሥራ አጥነት ምክንያት መዋያ የሌላቸው ወጣቶች የሚያዘወትሩዋቸው እነዚህ ፊልም ቤቶች ዕድሜያቸው ከ13 አመት ጀምሮ ያሉ ታዳጊ ወጣቶችም ከትምህርት ቤታቸው ሲለቀቁ እየተደበቁ ወደነዚህ የወሲብ ፊልም ማሳያ ቤቶች እየጎረፉ እንደሆነ ተዘግቦአል። ከቪዲዮ ቤቶቹ አጠገብ ደግሞ በወሲብ ስራ የሚተዳደሩ በትንንሽ ቤቶች ውስጥ ቆመው ደንበኞቻቸውን የሚጠብቁ ሴቶች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መበራከቱ ተገልጧል።

የፊልም ቤቶች እና የሴተኛ አዳሪዎች መበራከት ከአገሪቱ አጠቃላይ ችግር ጋር የሚታይ መሆኑን የማህበረሰብ ጥናት ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት አምጥቻለሁ በማለት የሚመጻደቀው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ  በአሁኑ ጊዜ ለወጣቶቹ የስራ እድል ለመፍጠርና በቂ የመዝናኛ ቦታዎችን ለማዘጋጀት ባለመቻሉ፣ ወጣቶቹ ከባህላቸው ውጭ የሆኑ የወሲብ ፊልሞችን ሲመለከቱና ለበሽታ ሲዳረጉ አይቶ እንዳላየ ያልፈዋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች የኑሮ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እጅግ አስከፊ የሆነ ገጽታ እየያዘ በመምጣቱ አብዛኛው ወጣት ባገኘው አጋጣም አገሩን ጥሎ በመሰደድ ላይ ይገኛል። ለመሰደድ እድልና አቅሙን ያላገኙ ወጣቶቹ ስራ ለመያዝ የገዢው ፓርቲ አባላት እንዲሆኑ መጠየቃቸው፣ ተምረው ስራ ለማግኘት የሚገጥማቸው ፈተና ጊዜያቸውን አላስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች እንዲያሳልፉ እንደሚያስገድዳቸው ጥናቶች ያሳያሉ።

## የወያኔ የንግድ ድርጅቶች ለእያንዳንዱ አርሶ አደር አስገድደው የሚሰጡትን የማዳበሪያ ዕዳ መክፈል ያልቻሉ አርሶ አደሮች በምሬት ነፍሳቸውን እያጠፉ እንደሆነ ተዘገበ

ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኙትን የአገሪቱን ትላልቅ የንግድ ዘርፎች የተቆጣጠሩት የወያኔ ንግድ ድርጅቶች መላውን የአገራችንን አርሶ አደር ያለውዴታውና ምርጫው በብድር ማዳበሪያ እንዲወስድ እያስገደዱት እዳውን መክፈል ሲያቅተው ደግሞ ከማሳውና ከቂየው እያፈናቀሉት እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

በመሬታቸው ለምነት ምክንያት ማዳበሪያ እንደማያስፈልጋቸው እየተናገሩና ለባለሥልጣናት አቤት እያሉ በየቀበሌው በተመደቡት የወያኔ ካድሬዎችና ግብርና ሠራተኞች ተገደው ማዳበሪያ እንዲወስዱ የተደረጉ በርካታ ገበሬዎች የጠበቁትን ያህል ምርት ሳያገኙ ሲቀሩ ዕዳቸውን ለመክፈል ሲሉ ለእርሻ የሚገለገሉባቸውን በሬዎች ሳይቀር እስከመሸጥ እየደረሱ ነው ተብሎአል። በማዳበሪያ ዕዳ ምክንያት በርካታ የአማራ ክልል አርሶ አደሮች ከእርሻ ማሳቸውና ከቄያቸው እየተፈናቀሉ እንደሆነ የዘገበው ዘጋቢያችን የደቡብ አገራችን ክፍል አርሶ አደሮችም ሰሞኑን በተመሳሳይ ችግር ውስጥ መውደቃቸውን ገልጾአል።

ወያኔ ትርፍ ለማግበስበስ ሲል በገፍ የሚያድለውን የማዳበሪያ ዕዳ ለመሰብሰባ የወረዳና የቀበሌ የመንግሥት መዋቅሮችን ይጠቀማል። እነዚያ የመንግሥት አካላት ደግሞ ዕዳቸውን በወቅት መክፈል ያልቻሉትን ገበሬዎች ንብረታቸውን ነጠቀው በመሸጥ ንብረት የሌላቸውን ደግሞ ከማሳቸውና ከቄያቸው በማፈናቀል እስከነቤተሰቦቻቸው ጎዳና ላይ ይወረውሩዋቸዋል።

በዚህ የማዳበሪያ ዕዳና በባለሥልጣናቱ የንብረት ንጥቂያ የተማረረ በደቡብ ክልል በጋሞ ጎፋ ዞን በቁጫ ወረዳ ነዋሪ የነበረ ጥላሁን ጤራ ባቦ የተባለ ገበሬ የኢህአዴግ ካድሬዎች በማዳበሪያ እዳ ሳቢያ ለሁለት ቀናት አስረው ሲያስጨንቁትና እዳውን በአስቸኳይ ካልከፈለ መሬቱን እንደሚነጥቁትና እንደሚያፈናቅሉት ነግረው ሲፈቱት ወዲያው ልጆቹን ይገፔ የትም አልበተንም፣ አልሰደድም ብሎ ራሱን አንቆ እንደገደለና፤ ሌላም ስሙ ለጊዜው ያልታወቀ ሰው ትልቅ ወንዝ ውስጥ እራሱን ከቶ መሞቱን የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን በትናንትናው ዜና ዘግባው ገልጾአል።

የማዳበሪያ ዕዳ ለበርካታ ገበሬዎች ከኑሮአቸው መፈናቀልና ህይወት መቀጠፍ ምክንያት መሆኑ ያስቆጣው የአካባቢው ህዝብ "እዳ ክፈሉ" እያሉ የሚመጡ የኢህአዴግ ካድሬዎችንና የወረዳ መስተዳደሮችን ወደቀበሌያቸው ላለማስገባት የወሰኑ ሲሆን፤ በዚያው በደቡብ ክልል በጋሞ ጎፋ ዞን የዑባ ማሌ ዘባ ቀበሌ ሊቀመንበርና ጸሐፊ ከህዝብ የተሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ከቁብ ባለመቁጠር እዳ ሊያስከፍሉ ሲሄዱ በአካባቢው ገበሬዎች ተደብድበው መገደላቸውን፣ በኡባ ማሌ ወረዳ ያላ ቀበሌ ውስጥም እንዲሁ የወረዳው የሚሊሺያ አዛዥ በአካባቢው ነዋሪዎች መገደሉን ኢሳት ዘግቦአል።

በተመሳሳይ ዜና በጋሞ ጎፋ ዞን በከሜላ ዛላ ዑባ ማሌ ወረዳ አንድ ፖሊስ በመገደሉ የተነሳ የአገዛዙ ሹማምንት ህዝቡን ማስጨነቅና ማስፈራራት ጀምረዋል:: በአሁኑ ጊዜም በጎፋ አካባቢ የገዜ ጎፋ ወረዳ ነዋሪዎች ማንኛውም የካቢኔ አባላት ወደ ቀበሌዎች ውስጥ እንዳይገቡ ወደ ጃውላና ባጋባርዛ የሚሄደውን መንገድ በእንጨት ግንድና አጠና በመዝጋት "ማዳበሪያ በፍላጎት እንጂ በግድ አይሰጠን፣ መሬታችን ለም ነው፣ ገንዘብ የለንም፣ እዳ አትቆልሉብን" በማለት ተቃውሞአቸውን እየገለጹ ነው።

በደቡብ ክልል በየጊዜው የሚታየው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ያሰጋው የወያኔ አገዛዝ የፌደራል ፖሊሶችን በአካባቢው በብዛት ማሰማራቱን ለማወቅ ተችሎአል።

## በኢትዮጵያ ውስጥ የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት፣ የለማኖች እና የወጣት ሴተኛ አዳሪዎች ብዛት በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ ተገለፀ

በኢትዮጵያ ውስጥ የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት፣ የለማኞች እና የወጣት ሴተኛ አዳሪዎች ብዛት በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ ለአንድ ዓለም ዓቀፍ ረድኤት ድርጅት ግብዓት እንዲሆን ጥናት ያካሄዱ ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ ባለሙያዎች ገለጹ። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ድህነትን አጠፋለሁ እያለ ድህነትን እየዘራ እንደሆነ እና የረድኤት ድርጅቶችም ሁኔታው ከአቅማቸው በላይ እየሆነ እንደመጣ ተናግረዋል።

ወጣቱ በሃገሩ ተስፋ እንዲያጣ በመደረጉ ለስደትና ለሱስ መዳረጉም አገሪቱን በቅርበት የሚከታተሉ ወገኖች ይገልፃሉ። ለምሳሌ በሰንበት ቀናት በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ የሚታየው የምዕመናን እና የነዳያን ቁጥር መሳ ለመሳ እየሆነ ነውም ይላሉ።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ኢኮኖሚያችን በየአመቱ አስራ አንድ ከመቶ በላይ እያደገ ነው በማለት በአለም አቀፍ አበዳሪዎችና ለጋሾች በሚሰጥ ገንዘብ የሚገነቡ መንገዶችን ርዝመት እና በብርሃን ፍጥነት የከበሩት የቀድሞ የህወሃት ታጋዮች ከህዝብ በተዘረፈ ገንዘብ የሚገነቡትን ህንጻዎች በማስረጃነት እያጣቀሱ ያቀርባሉ።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ስልጣን ከተቆጣጠረ ጊዜ ጀምሮ እየተስፋፋ ስለመጣው ድህነት የሚያማርሩ የአገሪቱ ዜጎች የመለስ ዜናዊ ወገኖች በህንፃ ላይ ህንፃ ሲገነቡ የኢትዮጵያ ህዝብ ወደ ፍጹም ድህነት እያሽቆለቆለ መሆኑ የሥርዓቱ ዘረኛነት አቢይ ማሳያ ነው ይላሉ። መለስ ዜናዊ በፍጥነት ካልተወገደ በስተቀር መላው ኢትዮጵያዊ በጥቂት የመለስ ዜናዊ ዘመዶች ርጥባን የሚጠብቅ ለማኝ መሆኑ አይቀርም በሚለው ትንበያ ብዙዎች ይስማማሉ።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በባርነት ወደ ሳውዲያረቢያ ለሚልካቸው ዜጎች . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መለስ ዜናዊና የቀድሞ ታጋይ ጓዶቹ ከህዝብ የሚዘርፉት የአገር ሃብት አንሶአቸው የአገሪቱን ለም መሬት ለባዕድ በርካሽ ዋጋ በመሸጥ የባለ ብዙ ሚሊዮን ሃብት ጌታ ለመሆን የበቁ ቢሆንም የደሃን ልጅ በባርነት ለአረብ በመሸጥ የሚገኘው ትርፍ እንዳይቀርባቸው ሲሉ በየቀኑ የሚሰጥ የቪዛ ቁጥር እንዲበራከት ስምምነት መፈጸማቸው በህወሃት ውስጥ የተሰባሰቡ ሰዎች አብዛኛው ሰው በስግብግብነት ወይም በጠላትነት ሌላውን ሲፈርጅ ከሚችለው የተለዩ ፍጥረቶች መሆናቸውን ያስመሰከሩበት ነው እንደ ታዛቢዎች አስተያየት።

በባርነት ወደ ሳውዲ አረቢያ ከተላኩት መቶ ሺዎች ውስጥ ምን ያህል እንደተገደሉ፣ ለአካል ስንኩልነት እንደተዳረገ፣ ባዶ እጁን ተጠፍሮ ከአገር እንደተባረረ፣ በየእስር ቤት እየተሰቃዩ እንደሚገኙ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለመግለጽ ፍቃደኛ አየደለም። ሌላው ቀርቶ አለም አቀፍ የዜና አውታሮች በኢትዮጵያዊያኑ ላይ በየአገሮቹ እየደረሰ ያለውን ስቃይ በስፋት እየዘገቡም ቢሆን ለወያኔ ቁብም አልሰጠውም።

በብርሃኑ ገብረክርስቶስ የሚመራ ቡድን በቅርቡ ለአባይ ግድብ ግንባታ ገንዘብ ለመሰብሰብ ወደ አረብ አገር በሄደበት ወቅት የስቃዩ ሰለባ የሆኑ ሴት እህቶቻችን አቅርበውት የነበረው ብሶት ሁሉንም እረፍት የነሳ እንደነበረ መዘገቡ ይታወሳል።

## ወያኔ የቀድሞ ሰራዊት አባላትን እና በጡረታ የተገለሉ ተቀናሽ ሰራዊት አባላትን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የተላኩት ባለስልጣኖች፣ "ለአገርና ለመንግስት ጸሮች ናችሁ በማለት ወታደሮቹን ለማስፈራራት ቢሞክሩም እንዳልተሳካላቸው ለማወቅ ተችሎአል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኤርትራን ህዝብና መንግሥት በአውሬነት እየሳለ ለኢትዮጵያዊያን ጠላት አድርጎ ለመሳል የሚያደርገው ጥረት ማንንም የማሳመን ሃይል እንደሌለው አገዛዙ ሳይቀር እየተረዳው የመጣ ሃቅ ሆኖአል የሚሉ በርካቶች ናቸው።

ወያኔ ወታደሮችን ለመቅጠር በተለያዩ አካባቢዎች በየጊዜው ተደጋጋሚ ማስታወቂያ ቢያወጣም እስካሁን የሚፈልገውን ያህል ተመልማይ ለማግኘት እንዳልቻለ ተያይዞ የደረሰን ዜና ያመለክታል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን፡፡

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org